# ሙልጭ አርጎ ካደን

ካለፈው አንማር ፣ ለመጣው ማራገብ
ማንነት አንጠይቅ ፣ አደግድጎ ማጀብ
ስንደግፍ በጭፍን ፣ ምንም ያለገደብ
መጠየቅን አንወድ ፣ ልብን ሰዶ መቅረብ
ምንም ላያካፋ ፣ እንኳንስ ለመዝነብ
አትንኩት እያሉ ፣ ነገር በመተብተብ
ጠያቂ ሲመጣ ፣ ስም ሰጥቶ ማዋከብ ።

እንዴትና ለምን ፣ ለሚለው ጠያቂ
ሹመት ከሚቋምጥ ፣ ተስፈኛ አዳማቂ
በአበላ ባይ ፣ አንጋች ፣ የወሬ ጠራቂ
ለተቺው መልስ የለው ፣ ሃሳብ አስታራቂ
መፍትሄ አያመጣ ፣ እሱ ብቻ አዋቂ
አሃዳዊ ስርዓት ፣ የጥንቱን ናፋቂ
እያሉ ማንጓጠጥ ፣ አድር ባይ ውዳቂ
እውነትን ማደባበስ ፣ ምንደኛ አለቅላቂ ።

እንናገር ካልን ፣ በግልፅ እንናገር
እውነት ተሸሽጋ ፣ ተደብቃ ላትቀር
ላያዋጣ ዘዴ ፣ ዙሪያ ከመሽከርከር
ቀን የወጣው አቋም ፣ የተሰማው ባገር
በጎሰኞች ስርአት ፣ እንዳይደራደር
ሲነጋ ሌላ አቋም ፣ ህዝብን ማደናገር
ከፍቶ ያሳየንን ፣ መልሶ መቋጠር ።

ፍቅር እየሰበከ ፣ አስመስሎ አቃፊ
በየመድረኩ ላይ ፣ አንድነት ለፋፊ
አንድ አመት ሳይሞላው ፣ አሽቀንጥሮ ገፊ
የዕሰስት ባህሪ ፣ ካለፈው አስከፊ
የሚጨበጥ የለው ፣ ሙልጭልጭ ቀጣፊ
ባፉ እየደለለ ፣ በተግባሩ አጥፊ ።

በአዲሳባ ዙሪያ ፣ ቅርሻት እያገሱ
እንዳበደ ውሻ ፣ ሰው እያስነከሱ
የደሃውን ጎጆ ፣ በላዩ ሲያፈርሱ
ውስልት በለመደ ፣ ቀጣፊ ምላሱ
ያፍራሹ አዴፓ ፣ ቁንጮና ንጉሱ
ብቅ አለ አቢቹ ፣ ቅቤ አፍ ልስልሱ
ያሰማራው ካድሬ ፣ አገርን ሲያምሱ
ሙልጭ አርጎ ካደን ፣ እንደማያውቅ እሱ ።

ታዛቢው

February 26, 2019